# ዝሆን ይኸውና ቢሉት፤ዱካውን አሳዩኝ አለ

እርቅይሁን (ከስድስት ኪሎ)

በ4ኛው ዙር አገራዊ ምርጫ ላይ ከሰላሳ ሚሊዮን ህዝብ በላይ ድምፁን ሰጥቶ ይበጀኛል ያለውን የፖለቲካ ፓርቲ በዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ መንገድ መርጧል፡፡ እስካሁን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ በተደረገው ጊዜያዊ ውጤት መሠረትም ኢህአዴግ ከሁለት ወይም ከሶሳት ቦታዎች በስተቀር በሌሎች በተወዳደረባቸው አካባቢዎች በሙሉ በከፍተኛ ድምፅ አሸናፊ መሆኑ ታውቋል፡፡ ኢህአዴግ በዚህ ምርጫ ላይ ያገኘው ውጤት ቀደም ሲል ከተደረጉት ምርጫዎች ሁሉ እጅግ በሰፊ ልዩነት ተፎካካሪዎችን ያሸነፈበት መሆኑ ታላቅ አግራሞትን ፈጥሯል፡፡

የዚህ ዓይነት ፍፁማዊ አሸናፊነት ፈረንጆች ‹‹ላንድ ስላይድ ቪክትሪ›› የሚሉት ያጋጠመውና ወደፊትም ሊያጋጥም የሚችልበት  ሁናቴ አልፎ አልፎ እንደሆነ በአንዳንድ ወገኖች ይገለፃል፡፡ ኢህአዴግ ምርጫውን በገዘፈ ልዩነት በርካታ ተፎካካሪዎችን ያሸነፈበት ዓይነት የምርጫ አፈፃፀምና ውጤት ሊያጋጥም ስለመቻሉ ማሰብ ለብዙዎች አዳጋች ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ነገር ግን በተጨባጭ ያየነውና የሆነው ይኸው በመሆኑ ውጤቱን አምነን እንድንቀበል ሁኔታው ግድ ይለናል፡፡ አንዳንዴ ያልተገመተና ያልተጠበቀ ክስተት  ተፈጽሞ ሲገኝ ቀደም ሲል የነበረንን ግምት የሚያፈርሰውም ቢሆን፣ ራስን ለእውነታው ማስገዛትና ክስተቱን ማስተናገድ የንፁህ ህሊና ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይህ ታዲያ መነሻ ሆነኝና  ግንቦት 15/2002 ስለተካሄደው አገራዊ ምርጫ ትንሽ ለማለት ፈለግሁ፡፡

ከምርጫው ቀደም ብሎ የምርጫው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል በሀገር ውስጥና በውጭ በሚገኙ በተለያዩ የፖለቲካና የታሪክ ምሁራን፣ የፖለቲካ ተንታኞችና ሚዲያወች እንዲሁም በህብረተሰቡ የተለያዩ ግምቶች ሲሰጡ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡እኔ ባጋጣሚ ካገኘኋቸው አስተያየቶችና ግምቶች የተረዳሁት የኢህአዴግ አሸናፊነት አይቀሬ እንደሆነ የሚገልጹት ያመዝኑ ነበር፡፡ ለዚህ

ግምታቸው መነሻ የሆኗቸውን ነጥቦች ሲዘረዝሩም አብዛኞቹ የተስማሙባቸው ኢህአዴግ ተግባራዊ እያደረጋቸው ያሉ መጠነ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴዎች በተለይ በመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ ለምሳሌ(በትምህርት፣በጤና በመንገድና ሌሎች የኮንስትራክሽን ግንባታዎች፤በቴሌ፤በኃይል ማመንጫ ግንባታዎች ወዘተ)፤ በተከታታይ እያስመዘገበ የመጣው አገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ወጣቶችንና ሴቶችን ተጠቃሚ ባደረጉ የጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ ፈጠራ ፕሮጀክቶች፣ለአገር ደህንነትባለው ቁርጠኛ አቋምና እስከ አምሥት ሚሊዮን የሚደርሱ አባላትን ከጐኑ ማሰለፉና የመሳሰሉትን በዋናነት አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተቃዋሚ ፓርቲዎች የውስጥ ክፍፍልና መሰነጣጠቅ፣ የአንጃዎች መፈጠርና እርስ በርስ መወነጃጀል፣ መወራረፍ፤ የጠራ ፖሊሲና ፕሮግራም ነድፎ ወደ ህዝቡ ያለመቅረብና ወዘተ የሚሉ ለኢህአዴግ አሸናፊነት ተጨማሪ ጉልበት ሊሆነው እንደሚችልም ሲነገር ቆይቷል፡፡

ከዚህ በተፃራሪው የቆሙ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የውጭ አካላት ደግሞ የኢህአዴግን አሸናፊነት ተቀብለው ነገር ግን ይህ የሚሆነው ኢህአዴግ ምርጫውን ሊያጭበረብር ይችላል የሚል የተሳሳተ ግምትና ድምዳሜ በመያዝ ይህን የተሳሳተ ስሌትና ውዥንብር እንደ ስልት ይዘው ወደ ህብረተሰቡ የሚረጩ ጽንፈኛና ጨለምተኛ አቋም የሚያራምዱ ወገኖችን መታዘብ ተችሏል፡፡ እነዚህ አካላት ከዚህ አልፈውም ምንም ይሁን ምን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሸናፊ የሚሆኑት ምርጫው በኢህአዴግ ከተጭበረበረ ብቻ እንደሆነ በመግለጽ የምርጫው ውጤት በራሳቸውና በራሳቸው አሸናፊነት ብቻ መቋጨት እንዳለበት ውጤቱን ከሂደቱ በፊት ራሳቸው በመወሰን ይህን ሀሳባቸውን እንደ ዋና መሪ መፈክርና ልዩ መታወቂያቸው ይዘው ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ኃላፊነት የጐደለው፣ አደገኛና ህገወጥ አካሄድ ስለነበር፤ ይህ አመለካከት መታረም እንዳለበት የሚያስገነዝብ የሰላ ትችትና ውግዘት ከሰላም ወዳድ ወገኖች በተከታታይ ሲቀርብ እንደነበርም አስታውሳለሁ፡፡ ድርጊቱ በእርግጥም መወገዝ እንደነበረበት በግሌ አምን ስለነበር አስተያየቱን እኔም ተጋርቸዋለሁ፡፡

በሌላም በኩል የአንዳንድ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋፊዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይም መድረክ አሊያም ኢዴፓ በጠባቡም ቢሆን አሸናፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምታቸውን ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም በወቅቱ እነዚህ ወገኖች ግምታቸውን የሚደግፍ ወይም የሚያጠናክር ተጨባጭ መረጃ ማቅረብ ያልቻሉበትን ሁኔታ ነበር መገንዘብ የተቻለው፡፡ በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳና ግልጽ የሚዲያ ክርክር ላይም አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህ ነው የሚባልና ውሀ የሚቋጥር አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ የሌላቸው መሆኑና አልፎ አልፎም ጭራሽ ፓርቲዎች የሚመሩበት ምንም ዓይነት የፖሊሲና የፕሮግራም አጀንዳ የሌላቸው መሆኑ በግልጽ የታየበትን ሁኔታ መታዘብ የቻልን ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ይልቅ ዋናውን አጀንዳ በመተው አንዴ ሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት በቀጥታ ኢህአዴግን ሲወነጅሉና በሀሰት ሲከሱ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ እርስ በራሳቸው ሲወነጃጀሉ፣ ሲነቃቀፉና ሲካሰሱ የነበሩበት ሁኔታ አመዝኖ ታይቷል፡፡

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ በተደረገው ጊዜያዊ ውጤት በግልጽ የሚያመለክተው ነገር ኢህአዴግ በብዙ መመዘኛዎች ከተፎካካሪዎቹ በእጅጉ ልቆ የተገኘበትና በአንፃሩም ተቃዋሚዎቹ በምንም መልኩ/ቢያንስ አሁን ባሉበት ሁኔታ/ ለህብረተሰቡ አማራጭ ሊሆኑ እንደማይችሉ ነው፡፡ ይህም በመሆኑም ነው ሁሉንም ባስደመመ ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ኢህአዴግ ተፎካካሪዎችን ያሸነፈው፡፡ ኢህአዴግ በመራጩ ህዝብ ላይ ባሳደረው ጽኑ ዕምነት ምክንያት ህብረተሰቡ ድምፁን ሰጥቶታል፡፡ ህብረተሰቡ በዚህ ላይ ጠንካራ የሚባል የጋራ መግባባት እንደያዘ በብዙ መልኩ ገልጿል፣ እየገለጸም ይገኛል፡፡

እንደኔ እንደኔ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከዘንድሮ የምርጫ ሂደትና ከውጤቱ ሊማሩበት ይገባል፡፡በ97ቱ ምርጫ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ላይ ከደረሰበት ሽንፈት ትምህርት አግኝቶ በዘንድሮው ምርጫ ውጤቱን ሊቀይር ችሏል፡፡በምርጫ ድምጻችንን ለኢህአዴግ የሰጠነው ለአምስት ዓመት እንጂ ለዘለዓለሙ ስላልሆነ፤ በዘንድሮው ምርጫ ድል ያልቀናችሁ ፓርቲዎች ለቀጣዩ የምርጫ ጊዜ የተሻለ አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ ካቀረባችሁልን ድምጻችንን የማንቸራችሁ ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡

ሌላው ቀርቶ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሂደትና የፖለቲካ ተሳትፎ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በርካታ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና ደጋፊዎች ውጤቱን አምነው በፀጋ በመቀበል የእንኳን ደስ ያለህ ግልጽ መልዕክት ለአሸናፊው ኢህአዴግ በማድረስ ላይ ይገኛሉ፡፡ እኔ ይህ ዓይነት የሰለጠነ የፖለቲካ አካሄድ በአገራችን መሠረት መያዝ መጀመሩን በመመልከቴ ሂደቱን ደግፌው ከቆሙና ከተደሰቱ የሀገሬ ዜጎች አንዱ ነኝ፡፡ በውጤቱም በጣም ኮራሁ፣ ሂደቱም በተለይም የፖለቲካ መቻቻሉ ጽኑ መሠረት ይዞ እንዲዘልቅ ከልቤ ተመኘሁ፡፡ ይህ ደግሞ የሁሉም ሰላም ወዳድና ለዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ መጐልበት የቆሙ ወገኖች ሁሉ ፍላጐት እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

በዚህ ምርጫ ላይ ኢህአዴግ የበላይነት ኖሮት በአሸናፊነት ሊወጣ እንደሚችል ገና ከመነሻው አመላካች የነበሩ ተጨባጭ እውነታዎች መኖራቸውን በማመልከት ግምታቸውን ሰጥተው የነበሩ ወገኖች በእርግጥም ልክ ነበሩ፣ ውጤቱም የመሰከረው ይህንኑ ነው፡፡ በእርግጥም ኢህአዴግ በዚህን ያህል ሰፊ የድምፅ ልዩነት ተፎካካሪዎችን ያሸንፋል ብሎ የጠበቀ እንዳልነበር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ ግን ተጠቃሚነቱን በተጨባጭ ካየው፣ ከተገነዘበውና በቀጣይም አገኛዋለሁ ብሎ ተስፋ ካደረገው ለውጥና ዕድገት አኳያ ተነስቶ ከግምት በላይ የላቀው መራጭ ድምፁን ለኢህአዴግ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ከሰላማዊ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የህዝብ ድምፅ የተገኘ አሸናፊነት በእርግጥም የሚያኮራ ቢሆንም ይህ ውጤት የሚያመላክተው አሸናፊው ፓርቲን ድርብ ድርብርብ ኃላፊነትን የሚያሸክም የህዝብ አደራ ነው፡፡ ይህንንም ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቅርቡ ለጋዜጠኞች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ በአጽንኦት ገልፀውታል፡፡

በዚህ ምርጫ ላይ ይነስም ይብዛ፣ ምክንያታዊ ይሁን አይሁን አንድና ሁለት ተብለው ለሚቆጠሩ ጥቂት የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አንዳንድ ወገኖችና ደጋፊዎቻቸው የአሸናፊነት ግምት ሰጥተዋቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡

ሆኖም ይህ ግምት በምክንያት የተደገፈ፣ ተጨባጭ ዕውነታውን ያላገናዘበ፣ የፓርቲዎችን ወቅታዊ ሁኔታ ያልተመለከተ እና የህብረተሰቡን ፖለቲካዊ ብስለትና የማመዛዘን ብቃት፤ ወቅታዊ አመለካከት፣ ግንዛቤና ፍላጐት በትክክል ያልመዘነ ስለነበር ውጤቱ በራሱ መንገድ ሄዶ እውነታውን ፍንትው አድርጎ አመላክቶን አልፏል፡፡ ከዚህ ሂደትም ብዙዎች ጠቃሚ ትምህርት ያገኙበታል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

እዚህ ላይ ኢህአዴግ ያልተጠበቀ ከፍተኛ የህዝብ ድምፅ አግኝቶ አሸናፊ በሆነበት የምርጫ ሂደት ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዴት በዚህ መጠንና ደረጃ ተሸናፊ ሊሆኑ እንደቻሉ አንዳንድ ትዝብቶችን ማንሳት አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡

በተፈጠረው ምቹ ዴሞክራሲያዊ መድረክ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የፖለቲካ ዓላማን በነፃነት የሚያራምዱ፣ ለዕድገትና ለለውጥ ራዕይ ሰንቀው የሚንቀሳቀሱ ጠንካራ የፖለቲካ ተፎካካሪዎች መኖር ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑ ፍፁም አጠያያቂ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከዚህ በተፃራሪ በስመ ተቃዋሚነት መልካም አፈፃፀሞችን በማጥላላት፣ በአሉባልታና በሀሰተኛ ክስ ጭፍን ጥላቻን ማንፀባረቅ፣ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አሻራ ስላረፈበት ብቻ የተሰራ ልማትንና ግንባታን እንደሌለ አድርጐ ማቅረብ አዎንታዊ የዓላማ ስኬትን አያስገኝም፡፡

ከዚህም ሌላ ለህብረተሰቡ ተጨባጭነት የሌለው የተስፋ ቃል በመመገብ፣ ጥቃቅን ስህተቶችንና ግድፈቶችን ከልክ በላይ በመለጠጥና በማግዘፍ፣ አንዳንዴም ያልተፈጠረ ችግርን ያለ በማስመሰል ህብረተሰቡን ውዥንብር ውስጥ በመክተትና ሕጋዊ አካሄድን ባለመከተል ሀቀኛና ትክክለኛ የሕዝብ ድጋፍ አገኛለሁ ብሎ ለመንቀሳቀስ መሞከር ከውድቀት በመለስ የትም ሊያደርስ እንደማይችል ጽኑ ዕምነት ሊያዝበት ይገባል፤በተግባርም የታየው ይኸው ነው፡፡ በህዝቦች መብትና ጥቅም ላይ ያነጣጠረ ፖለቲካዊ ቁማር ለመጫወት መሞከር አደጋ አለው፣ አገርን ይጐዳል፣ከዚህ ጋር በተያያዘም ህጋዊ ያልሆነ አካሄድ ለመከተል መሞከርም እንደሁኔታው የግልና የጋራ የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ታዲያ ቀደም ባሉትም ሆነ በዚህኛው ምርጫ ላይ ከላይ የተጠቃቀሱት ጉድለቶችና ችግሮች ይነስም ይብዛ በብዙዎቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ በግልጽ የተንፀባረቁ እንደነበሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የጠራና የነጠረ ህዝባዊ ዓላማና ግብ ይዘው ባለመንቀሳቀሳቸውም በራሳቸው ውስጥ ተደጋጋሚ ክፍፍልና መሰነጣጠቅ አጋጥሟቸዋል፡፡ ይህም ለአብዛኛው የድክመታቸው ምንጭ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ይመስለኛል፡፡ የህዝብን ስሜት ይኮረኩራሉ ተብለው በአንዳንድ ተቃዋሚዎች ሲነገሩ የነበሩ አቋሞች የሕዝቡን ስሜትና ፍላጐት እንደማይወክሉ ህዝቡ ግልጽ መልዕክቱን በድምፁ አረጋግጧል፡፡ የህብረተሰቡን ፍላጐትና ዓላማ የማይወክል ማንኛውም ሀሳብ ምን ያህል ተቀባብቶና ወዝቶ ቢቀርብ የህዝቡን ስሜት እነሱ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ሊመሩት እንደማይቻላቸው የምርጫው ውጤት በግልጽ ያመላከታቸው ይመስለኛል፡፡

ይህን ዕውነታ በድፍረትና ከልብ አምኖ አለመቀበል ስህተትን ዘርቶ ስህተትን ማጨድ ይሆናል፡፡የራስ ስህተትን አውቆና በግልጽ ተቀብሎ ለማረምና ለማስተካከል መንቀሳቀስ ከህብረተሰቡ ከበሬታን ያስገኛል፡፡ ዕውነታን ደፍሮ ለመቀበል ፈቃደኛነቱ ከጎደለ ግን ነገሩ ሁሉ “ዝሆን ይኸውና ቢሉት ዱካውን ካላየሁ ኣላምንም” አለ የተባለውን ዓይነት ሰው ይሆንና ተዓማኒነትንና ተቀባይነትን በእጅጉ ያዳክማል፤ በራስ የመተማመንና ራስን ችሎ የመቆም አቅምንም ያሳጣል፡፡

ይህ አሁን በተቃዋሚዎች ጐራ ያጋጠመ ፖለቲካዊ ሽንፈት ‹‹እኔማ ካልተመረጥኩ...›› የሚል ግትርና ኢ- ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ከትግል የሚያሸሽ ወይም ደግሞ ከህጋዊ አካሄድ ያፈነገጠ እንቅስቃሴ ለማድረግ መንስኤ ሊሆን አይችልም፤አይገባምም፡፡ ከዚህ ይልቅ የራስ ድክመትን አምኖ በመቀበል የህዝብ ፍላጐትን መሰረት ያደረገ የተሀድሶ ለውጥ ማድረግና ህዝብን ማዳመጥ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ህዝብን እኔ ብቻ አውቅልሀለሁ በሚል ጠባብና ጭፍን አመለካከት ለማሞኘት መከጀል ምንም ያህል እርቀት ሊያስኬድ አይችልም፡፡ ራስን ብቻ ከህዝብ በላይ አዋቂ አድርጐ በማሰብና ህዝብ ለራሱ እንደማያውቅና መወሰን እነደማይችል

በመቁጠር ፍላጐቱ በሌሎች እንደሚወሰንለት ማሰብና ራስን አግዝፎ ማዬት አዋጭ የፖለቲካ አካሄድ አይደለም፡፡ ራስን ብቻ በማዳመጥ ከእኔ በላይ ላሳር የሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ይዞ ለመንቀሳቀስ መሞከር ከህዝብ ይነጥላል፡፡ ህዝብ ያውቃል፣ ይወስናል፣ ይፈርዳልም፡፡ ራስን ለህሊና እና ከሁሉም በላይ ለህዝብ ፍላጐት፣ መብትና ጥቅም ማስገዛት፤ ህዝብን ማድመጥና ፖለቲካዊ መቻቻልን ማጐልበት የትልቅነት አንዱ መለኪያ ነው፡፡የራስ ድክመትንና ስህተትን በሌላ ስህተት ለመሸፈን መሞከር ትርፉ የባሰ ውድቀትን መጋበዝ ነው፡፡

በቅርቡ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ በሰጡት ጋዘወጣዊ መግለጫ ላይ ህዝብ ድምጹን በጭፍን እንደሰጠና ነገሮችን ማመዛዘን እንደማይችል ዓይነት እንደምታ ያለው ንግግር ሲያደርጉ አደመጥኩ፡፡በዕውነቱ ግለሰቡ የፈለጉትን የመናገር መብት ቢኖራቸውም የመራጩን ህዝብ ከብርና ስሜት የሚነካ መሆን ግን የለበትም፡፡

በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ፓርቲም አሸናፊ መሆን በራሱ ብቻ ግብ እንዳልሆነና ከዳር እንደማያዘልቅ ተገንዝቦ፣ የህዝብ ችግሮችን ዕለት ተዕለት በመከታተልና ህዝብን በማድመጥ መፍትሔ ለመስጠት ከምንጊዜውም በበለጠ ቁርጠኝነት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድም የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሴዎችን አጠናክሮ የማስቀጠል፤ መልካም አስተዳደርን እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የማስፈንና በየደረጃው ሙስናን የመዋጋት ጥረቶች ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡የአሸናፊነት ፋይዳው በትክክል ሊመዘን የሚችለው እፈጽመዋለሁ ያሉትን በተግባር አድርጎ ሲገኙ ነውና ህብረተሰቡ እስካሁን ከተቀዳጀው ውጤት በቀጣይ የበለጠ የሚጠብቅ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝበት ይገባል፡፡

አሸናፊው ኢህአዴግ ቀደም ሲል የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሰዎችንና ስኬቶችን በሁለንተናዊ መልኩ እያጎለበተ የበለጠ ስኬትን በተጨባጭ በማሳየት የህዝብንና የአገርን ተጠቃሚነት ይበልጥ እያጎለበተ መቀጠል ይኖርበታል፡፡የገባውን ቃል ጠብቆም ይንቀሳቀሳል ብለን እናምናለን፡፡ የህብረተሰቡን የልማት ተነሳሽነት ይበልጥ በማጎልበትና በማስፋት የአገራችን ህዳሴ ዕውን ይሆናል የሚል ሰፊ የህዝብ ተስፋና ዕምነት ስላለ ይህን በቁርጠኝነት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎችም አገራዊ አጀንዳዎችና ጉዳዮች ሁሉ እነሱንም በቀጥታ  የሚመለከት መሆኑን ተገንዝበው የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ለአገራዊ ዓላማ ስከኬትም ሁላችንም በመተማመን በአንድነትና በፍጹም አገራዊ ስሜት በጋራ  መንቀሳቀስ ይኖርብናል እያልኩ ለዛሬ በዚህ ላብቃ፡፡